ህጻናትን በአዎንታዊ ሁኔታ ስርአት ማስያዝ

## ማውጫ

መግቢያ 2

ስልጠናውን በተመለከተ አጠቃላይ መመሪያ 3

1. ሥርአት ማለት ምን ማለት ነው? 6

1.1. "ሥርአት ማስያዝ" ምን ማለት ነው?.....7

1.1.1 "ሥርዓት ማስያዝ" ትክክለኛ ትርጉሙ ምንድነው?.....7

1.2. ህጻናትን ሥርዓት ማስያዝ ለምን ያስፈልጋል?.....8

1.3. አንድ ህጻንን በሥርዓት አንጾ ማሳደግ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ምንድናቸው?.....8

1.4. በህፃናት ባህሪያት ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ነገሮች.....9

2. የቅጣትን ምንነት መገንዘብ12

2.1. የቅጣት እና የአወንታዊ ስርዓት ማስያዝ ልዩነት.....13

2.2. ቅጣት ምንድነው?.....13

2.3. ቅጣት ከህጻናት አንጻር ሲታይ.....14

2.4. የቅጣት አይነቶች.....14

2.5. ህጻናትን መቅጣት የሚያስከትላቸው ችግሮች.....15

2.6. የህፃናት ቅጣት በኢትዮጵያ.....16

2.7. በህብረተሰባችን በወላጆችና በመምህራን ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው እና በተለምዶ ቅጣትን የሚያስከትሉ የልጅ ባህርያት.....17

2.8. ስነሥርዓት እና የቅጣት ልዩነቶች ማጠቃለያ ለወላጆች/አሳዳጊዎች.....20

3. አሉታዊና አወንታዊ ስነስርአት ማስያዣ መንገዶች 21

3.1. አሉታዊ የስነስርአት ማስያዣ መንገዶች.....21

3.2. አወንታዊ የስነስርአት ማስያዣ መንገዶች.....23

3.3. ተግባራዊ ልምምድ.....26

4. ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ሕፃናትን እንዴት በአዎንታዊ መንገድ ስነስርአት ማስተማር ይችላሉ 31

5. ቁልፍ መልእክቶች 35

**መቅድም**

ይህ መጽሃፈ ዕድ በሀገራችን ኢትዮጵያ  ሕጻናትን ሥርዓት  እንዴት ማስተማር እንደሚቻል  የወላጆችንና የመምህራን የግንዛቤ ደረጃ በሥልጠና  ለማሳደግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ሕጻናት የነገ ትውልድ ተረካቢ ናቸው። ከዚህ አንጻር የወደፊት የትውልድ ኃላፊነታቸውን በያገባኛል የዜግነት ስሜት እንዲወጡ ከተፈለገ ይህን ለማድረግ የሚያስችል ማንኛውም መልካም አጋጣሚ ወይም ዕድል አስቀድሞ ሊመቻችላቸው የግድ ይላል።

ለብዙ ዓመታት የተደረጉ የጥናት ግኝቶች  እንደሚያሳዩት  በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ለሕጻናት የሚደረገው እንክብካቤና የሚሰጠው ትኩረት የሕጻናቱን የወደፊት አጠቃላይ ሕይወትና ስብእና  ከመወሰን አኳያ የሚኖረው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው። በልጆች እንክብካቤ የወላጆችና የመምህራን ሚና ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል።

በሀገራችን በተለምዶ ወይም ሲወርድ ሲዋራረድ በመጣው የሕጻናት አስተዳደግ ልማድ ልጆች እንዳይርባቸውና እንዳይጠማቸው እንዲሁም እንዳይበረዳቸው ከማድረግ ውጪ ለአካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሮአዊና ማህበራዊ ሕይወታቸው እድገት ብዙ ትኩረት አይሰጥም። በእርግጥም ልጆችን ማብላት፤ ማጠጣትና ብርድ መከላከል ትልቅ እንክብካቤ ቢሆንም  ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ብዙ  ጉዳዮች አሉ።

የልጆችን መብት የማክበር ጉዳይ እንዲሁም ልጆችን ስነስርአት ለማስተማር  የምንጠቀምባቸው መንገዶች ትኩረት ተነፍገው የቆዩ ጉዳዮች ናቸው። ህጻናትን እንደ ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ባለመብት መሆናቸውን ያለመገንዘብና፤ ህፃናት ካልተቆነጠጡ/ካልተቀጡ ስርአት አይዙም የሚለው አመለካከት በኅብረተሰቡ ዘንድ ሠርፆ በመቆየቱ በህፃናት መብትና ስነስርአት ማክበር ዙሪያ የተለያዩ ችግሮች ይታያሉ። ለምሳሌ ያህል በህጻናት እንቅስቃሴ ላይ በጣም ገደብ የማብዛት፣ ሕጻናት በአዋቂዎች ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውን ባህርያት ሲያሳዩ የመምታት/የመቅጣት እርምጃዎች የሚወሰዱት ሕጻናት የተበላሸ ባህርይ ይዘው እንዳያድጉ ከሚል አመለካከት የተነሣ ነው። ይህ በተሳሳተ አመለካከት ህጻናትን ስነ ስርዓት ለማስተማር የሚወሰደው እርምጃ በህጻናት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሲያሳርፍ ቆይቷል።

የዚህ መጽሀፈ እድ ዓላማ ህጻናትን ሥርዓት ለማስተማር በሕብረተሰቡ ዘንድ ሥር ሰደው የቆዩትን ጎጂ አመለካከቶችን ለመቀየር የሚደረጉ ጥረቶችን ለማገዝ የሚያስችሉ ሌሎች አማራጭ ዘዴዎችን ማቅረብ ነው። ስለዚህም ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች እንዲሁም መምህራን  ይህንን መጽሀፈ እድ በመጠቀም ህጻናትን በአወንታዊ መንገድ ስነ ስርአት ማስተማር ይችላሉ። ስኩል ሬዲነስ ኢኒሼቲቭ ይህንን መጽሀፈ እድ በማስተማሪያነት አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች በማቅረቡ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል።

ዶ/ር ምኒልክ ደስታ አርጋው

የአእምሮ ህክምና ባለሙያ እና የፕሮጀክቱ መሪ

## የቃላት መፍቻ

በመጽሐፈ እዱ ውስጥ የሚገኙ ሙያዊ ማብራሪያ የሚያሻቸው ቃላት ወይንም ጽንሰ ሐሳቦች እንደሚከተለው በአጭሩ ተቀምጠዋል። ስለዚህም አመቻቾች ይህንን አስቀድመው ሊመለከቱት ይገባል።

መጽሐፈ እድ ፦ አንድን ተግባር ለማከናወን መከተል የሚገባን አሠራርና ቅደም ተከተል በየደረጃው ለማሳየት የተዘጋጀ መጽሐፈ

ማእቀብ ፡ አንድን ወይንም የተለያዩ ተግባራትን እንዳያከናውኑ የሚጣል ገደብ

መገናኛ ብዙኃን ፡ በጋዜጣ ወይንም በመጽሔት የታተሙ ጽሑፎች፣ በድምፅ በሬድዮ ወይንም በምስል ወድምፅ በቴሌቪዥን መልእክት ለማስተላለፍ የሚችሉ መሣሪያዎች

ዘረመል ፡ ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ባሕርያት የሚወስን ከወላጆች የሚወረስ ተፈጥሯዊ ቅመም

አሉታዊ ሥነ ሥርዓት ማስተማሪያ መንገድ፡ በኃይል ወይንም በጉልበት ወይንም በማስፈራራት ሕጻናትን ሥነ ሥርዓት ለማስተማር የምንጠቀምበት ዘዴ

አወንታዊ ሥነ ሥርዓት ማስተማሪያ መንገድ፡ በሕጻናት ላይ አካላዊ፣ ስሜታዊና አእምሮአዊ ጉዳት ሳያደርስ ሥነ ሥርዓት ለማስተማር የሚያስችል ዘዴ

ጡብ አጫሪነት፡ ግጭት ወይንም አለመግባባት ቀስቃሽነት

## ስልጠናውን በተመለከተ አጠቃላይ መመሪያ

የስልጠናው አላማ፡ በስልጠናው መጨረሻ ወላጆች/አሳዳጊዎች ህፃናትን ስነስርአት ለማስያዝ የአሉታዊ (ጠቃሚ ያልሆነ) ዘዴዎችን ጉዳትና የአወንታዊ (ጠቃሚ በሆነ) ዘዴዎችን ምንነትና ልዩነት ይገነዘባሉ።

የስልጠናው ተሳታፊዎች

የስልጠናው ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የሚጠበቁት መምህራን፣ ህፃናትን በሚንከባከቡ ድርጅቶች የሚሰሩ ሰራተኞች፤ እንዲሁም ወላጆች እና አሳዳጊዎች ናቸው።

ያለፈውን ቀን ውይይት መከለስ

በየስልጠናው መጀመሪያ ላይ ሁለት ተሳታፊዎች እየተመረጡ ባለፈው ስልጠና የተማሩትን ፍሬ ሀሳቦችን እንዲናገሩ በአወያዮች/በአስልጣኞች ይጠየቃሉ። ለምሳሌ፦

1. ባለፈው የተወያየንባቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
2. ባለፈው ከተወያየንበት ርእሰ ጉዳይ አንፃር በቤታችሁ ከልጆቻችሁ ጋር ምን አደረጋችሁ? ያጋጠማችሁ ችግር ነበር ወይ?
3. ያለፈውን ትምህርት ለጎረቤቶቻችሁ አካፈላችሁ?

ቅድመ እና ድህረ ስልጠና ምዘና

ያለፈውን ስልጠና ለማስታወስ ከሚደረገው ተግባር ቀጥሎ እለቱ ስልጠና ከመጀመሩ በፊት ለተሳታፊዎች የቅድመ-ስልጠና ምዘና ይሰጣቸዋል። በስልጠናው የቀሰሙትን እውቀት ለመገምገም ደግሞ በያንዳንዱ ስልጠና መጨረሻ የድህረ-ስልጠና ምዘና ላይ ይሰጣል።

አጠቃላይ የስልጠና ደንቦች፤

በስልጠናው የመጀመሪያ ቀን የሚከተሉትን የስልጠናውን ህጎች ለተሳታፊዎቹ ያሳውቋቸው

- የሰልጣኞች አቀማመጥ በግማሽ-ክብ ቢሆን እንደሚመረጥ ማሳወቅ
- የአወያይ እና የተሳታፊዎች ትውውቅ ማካሄድ
- በሰአት መገኘት
- በስልጠናው ወቅት የሞባይል ስልክ ጥሪን ድምፅ አልባ ማድረግ
- በእያንዳንዱ የስልጠና ክፍለ-ጊዜ ጊዜ መገኘት
- ንቁ ተሳትፎ ማድረግ
- የሌሎች ሰዎችን ሃሳብ ማክበር
- የአስታዋሽ ምርጫ፡ በየእያንዳንዱ ቀን መጀመሪያ ላይ ባለፈው ቀን የተማሩትን ትምህርት በተመለከተ ለተሳታፊዎች ለማስታወስ በአጭሩ ገለፃ የሚያደርጉ ሁለት ተሳታፊዎችን መሰየም፡ 5 ደቂቃ የማቅረቢያ ጊዜን መወሰን
- የስልጠና ቦታውን ማስተካከል - በየእያንዳንዱ ቀን መጀመሪያ ላይ ለአስር ደቂቃ ያህል የስልጠናው አስተባባሪዎች የስልጠናውን ቦታ ያመቻቻሉ
- ሰአት ተቆጣጣሪ መምረጥ

የሚያስፈልጉ ቁሶች

- በህፃናት እድሜ ደረጃ የተዘጋጁ የተረት ወይም የታሪክ መፅሃፍትእና ስእሎች
- ንፁህ የመፃፊያ ሰሌዳ / ፍሊፕ ቻርት
- ማርከር/ጠመኔ
- ብዕር እና የማስታወሻ ደብተር
- በራሪ ፅሁፎች

በእያንዳንዱ ስልጠና መጨረሻ አወያዮች/አሰልጣኞች ማስታወሻ መያዝ አለባቸው

በእያንዳንዱ ስልጠና መጨረሻ ላይ አወያይ ስለ ውይይቱ ሂደት ማስታወሻ እንዲይዙ ይጠበቃል። ለውይይቱ በሚያደርጉት ዝግጅት ወይንም በውይይት ሂደት ውስጥ ነጥረው የወጡና በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሊካተቱ ወይም በድጋሚ ሊጤኑ የሚገቡ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ ያስፈልጋል። እነዚህ ፍሬ ሀሳቦች ይህንን ሰነድ ወደፊት የበለጠ ለማዳበር ይረዳሉ። በዚህ ኤነት የተያዙ ማስታወሻዎች ስኩል ሬዲነስ ኢኒሽቲቭ ከትምህርት፣ ጤና፣ ሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በመተባበር በሚያዘጋጇቸው የአሰልጣኞች ስልጠና ላይ ቀርበው ውት ከተደረገባቸው የማሰልጠኛ መፅሀፈ እዱን ለማሻሻልና ምሉእ ለማድረግ እጅግ ይጠቅማሉ

## ህጻናትን በአዎንታዊ ሁኔታ ስነ ስርአት ማስያዝ

ይህ ስልጠና ስለ ሕጻናት የስነ-ሥርዓት አያያዝ መሠረታዊና ዝርዝር የሆኑ መረጃዎችን ያስረዳል

መርሃ ግብር

| ይዘት | የማስተማሪያ ዘዴ | ሰዓት |
|---|---|---|
| የቅድመ ስልጠና ምዘና | የጥያቄ ወረቀቶቹን መበተን | 15 ደቂቃ |
| የስልጠናው ዓላማ | ማንበብና መወያየት | 2 ደቂቃ |
| ስነሥርዓት ማለት ምን ማለት ነው? | ጥያቄና መልስ እና ገለፃ | 10 ደቂቃ |
| የቅጣት ምንነትን መገንዘብ | ጥያቄና መልስ እና ገለፃ | 10 ደቂቃ |

| | | |
|---|---|---|
| ልጆችን ስነስርአት ማስያዣ መንገዶች | ጥያቄና መልስ እና ገለፃ | 15 ደቂቃ |
| ወላጆች ሊያደርጓቸው የሚችሏቸው ነገሮች | ማንቡብና መወያየት | 10 ደቂቃ |
| ቁልፍ መልዕክቶች | ማንቡብና መወያየት | 10 ደቂቃ |
| የድህረ-ስልጠና ምዘና | የጥያቄ ወረቀቶቹን መበተን | 15 ደቂቃ |

የሥልጠናው ዓላማ

ሰልጣኞች ከሥልጠናው በኋላ ፦

- ተገቢ የሆኑና ያልሆኑ ባሕርያትን ይለያሉ።
- የአዎንታዊ ሥርዓት ማስያዣ  ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ፡፤
- የቅጣትን ምንነትና ዓይነቶችን ይለያሉ።
- ቅጣት የሚስከትላቸውን ችግሮች ይገልፃሉ።
- ሥርዓት ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ።
- ሕጻናትን ስነሥርዓት ማስተማሪያ ዘዴዎችን ይለያሉ።
- ገንቢ ያልሆኑ ሥርዓት ማስያዣ ስልቶችን ይገነዘባሉ።

## 1. ስነሥርአት ማለት ምን ማለት ነው?

አወያይ

መልስ ከመስጠትዎ በፊት ተሳታፊዎቹን ‹ስነስርአት ማለት ምን ማለት ነው?› ብለው ይጠይቋቸውና መልሱን በሰሌዳ ላይ ይፃፉ

አወያይ፡-መልስ ከመስጠትዎ በፊት ተሳታፊዎቹን በተለምዶ የሚታወቀው “ስነሥርዓት ማስያዝ” ምን ማለት ነው? ብለው ይጠይቋቸውና መልሱን በሰሌዳ ላይ ይፃፉ።

ለምሳሌ

ያህልም “ይህ ሕጻን ሥርዓት ሊይዝ ይገባል” ለሚለው አባባል፡ “ይህ ልጅ መመታት ወይም መቀጣት አለበት” የሚል ትርጉም ይሰጠዋል ።

ይህ ትርጓሜ በቅን ልቦና የተያዘ ቢሆንም ስህተት ነው። ትክክለኛ ትርጉሙን ከታች 1.1.1 ስር ያለውን ያንብቡላቸው

<u>ትርጉም</u>

ስነስርአት ማለት ማህበራዊና ባህላዊ ተቀባይነት ያለው አንድ ሰው በተለያየ ሁኔታና ቦታ እንዲያሳይ የሚጠበቅበት ባህርይ ነው። ስነስርአት አንድ ሰው በባህሉ ተቀባይነት ያለውን ባህርይ በመላበስ ተቀባይነት የሌለውን ባህርይ ከማሳየት የሚታቀብበት መንገድ ነው። ተገቢ ወይንም ተገቢ ያልሆነ ስርአት ምንነትና መገለጫ ከባህል ባህል እንዲሁም ከእድሜ እድሜ ይለያያል::

ህፃናት በወላጆቻቸው ወይንም በአሳዳጊዎቻቸው ወይንም በባህላቸው እንዲያደርጉ፣ እንዲናገሩና እንዲፈፅሙ ወይንም እንዳያደርጉ፣ እንዳይናገሩና እንዳይፈፅሙ የተማሩትን ወይንም የተሰጣቸው መመሪያ ሲፈፅሙ ስነ ስርአት ያላቸው ህፃናት ይባላሉ። ህፃናት ስነ ስርአትን የሚማሩት ከቤተሰባቸው ነው።

## 1.1. **”**ስነሥርአት ማስያዝ**”** ምን ማለት ነው**?**

በዘልማድ እንደሚታወቀው ሥርዓት ማስያዝ ማለት ልጆች ከወላጅ ወይም ከመምህር ወይም ከሌላ የሚደርስባቸውን ዱላ ወይም ሌላ አካላዊ ቅጣት ፈርተው ያልተፈለገ ጠባይን እንዲተዉ ማድረግ መሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን ይህ ትክክለኛ ትርጉም አይደለም።

### **1.1.1 “**ሥርዓት ማስያዝ” ትክክለኛ ትርጉሙ ምንድን ነው**?**

ልጆችን ሥርዓት ማስያዝ ማለት የሥርዓት አተገባበርን ወይም ልጆች የሚፈለግባቸውን ጠባይ እንዲያሳዩና የሚፈለገውን ነገር እንዲያደርጉ እና የማይፈለግ ነገርን እንዳያደርጉ፤ ይህንንም ጠባይ በዘላቂነት እንዲተገብሩት በፍቅር በማስተማርና በአርአያነት እያሳዩ ማብቃት ነው።

አወያይ፡ ለዚህ ርእስ መልሱን ከመንገርዎ በፊት ተሳታፊዎቹን የሚያስቡዋቸውን ምክንያቶች ይጠይቁና መልሱን በሰሌዳ ላይ ያስፍሩ። መልሶቻቸውን ከተሰጠው ማብራሪያ ጋር እያነፃፀሩ ያስረዱአቸው።

## **1.2.** ህጻናትን ስነሥርዓት ማስያዝ ለምን ያስፈልጋል?

የስነ ሥርዓት ግንዛቤ የመጨረሻው ግብ ህጻናት የራሳቸውን ጠባይ ተረድተው ለምርጫቸው ኃላፊነትን የሚወስዱበት፣ ለራሳቸውና ለሌሎች ክብር የሚሰጡበትና በራሳቸው ተነሳሽነት እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ሂደት ነው ።

የህፃናት ስነ ስርአት በአንድ ተግባር ብቻ የሚመጣ ለውጥ ሳይሆን በሂደት የሚገነባ ውጤት ነው። ህፃናት የራሳቸውን ስነ ምግባር የሚያዳብሩት በወላጆች በተከታታይ በሚሰጣቸው ትምህርትና መመሪያ ነው። ወላጆች ያለማቋረጥ በሚያደርጉት ምልከታ፣ ለልጆቻቸው በሚያስቀምጡላቸው መመሪያና ህፃናቱ መመሪያ ሲጥሱ በተከታታይ በሚወሰዱ የማረሚያ እርምጃዎች ህፃናት ራሳቸውን ስነ ምግባር የማስተማር ክህሎት ያዳብራሉ። የህፃናት የስነ ስርአት ግድፈትን የማረሚያ መንገዶች አወንታዊ ወይንም አሉታዊ ሊሆኑ ይችላሉ።

አወያይ

ህጻናትን ስነ-ምግባር ማስያዝ ማለት በማስተማርና አርአያ በመሆን ተቀባይነት ባለው ባህርይ ኮትኩቶ ማሳደግ ማለት ነው እንጂ የማንፈልገውን ባህርይ ሲያሳዩ በመቅጣት አይደለም።

ህጻናትን ስርአት ማስያዝ የሚቻለው በፍቅርና በትእግስት ነገር ግን በቁርጠኝነት አሰልጥኖ በማብቃት ለደንብና ለሥነ-ምግባር ተገዥ እንዲሆኑ በማድረግ እንጂ በቅጣት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል።

## **1.3.** ህጻናትን በስነሥርዓት አንጾ ማሳደግ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

- የምንፈልገውን ጠባይ እንዲኖራቸው ይረዳል።
- ራሳቸውን መቆጣጠርና መጠበቅ የሚያስችላቸውን ግንዛቤ ለማዳበር ያግዛቸዋል።
- ህጻናት በራሳቸው ለመሥራት፣ ለመማር እና እነዚህንም ለማሳካት የሚያደርገውን ጥረትና መነቃቃት ያቀላጥፍለታል።
- ህጻናት ተፈላጊ ባህርይን በሚያሳዩበት ወቅት አድናቆትና ሽልማት ሲያገኙ ራሳቸውን በደንብ እንዲጠብቁና እንዲቆጣጠሩ ያስችላቸዋል።
- ለራሳቸው የሚሰጡት ጤናማ ግምት ከፍ እንዲል ያደርጋል።
- የኃላፊነቱ ምንጭ በቀጥታ ራሳቸው መሆናቸውን ሲገነዘቡ  በሥራቸው ይረካሉ እንዲሁም ህይወታቸውን የመምራት ክህሎት ያዳብራሉ።

## **1.4.** በህፃናት ባህሪያት ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ነገሮች

ህፃናት የራሳቸውን የተለየ ስነ ምግባር ይዘው የሚያድጉት በሂደት ነው። የህፃናት ስነ ምግባር የተለያዩ ተፅእኖዎች ውጤት ነው። ተፅእኖ የሚያደርጉት ምክንያቶች ከህፃናቱ፣ ከወላጆችና ከአካባቢያቸው ሊመነጩ ይችላሉ። እነኚህ በግለሰብ ስነምግባር ላይ ተፅእኖ ከሚያደርጉት ዋና ዋናዎቹ ቀጥለው ቀርበዋል።

ሀ)ተፈጥሮአዊ ምክንያት

አወያይ

በዚህ ክፍል ውስጥ ‹ተፈጥሮአዊ›  ማለት አንድ የሴት እንቁላል ከአንድ የወንድ ዘር ጋር ከሚገናኙበት ቅፅበት አንስቶ ህፃን ተወልዶ ከሰዎች ጋር ማህበራዊ ግንኙነት እስኪጀምር ባለው ጊዜ በግለሰቡ ውስጥ የሚከናወኑ የተፈጥሮ ሂደቶችን ይመለከታል። እነኚህ የተፈጥሮ ሂደቶች በህፃናት ባህርይ ላይ የራሳቸው የሆነ ተፅእኖ አላቸው። በተለይ በዘረመል እና በነርቭ ስርአት እድገት ሂደቶች ላይ በሚገጥማቸው ችግር ህፃናት የተለየ ባህርይ ሊያሳዩ ይችላሉ።

ለ)የወላጆች ወይንም የአሳዳጊዎች ተሳትፎ

አወያይ

ወላጆች በህፃናት ጠባይ ላይ ጉልህ ተፅእኖ ያደርጋሉ። ይህን ስንል ወላጆች ልጆቻቸውን በተለያዩ አጋጣሚዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው፣ እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው ያስተምራሉ። ይህ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያስተምሩት ስነ ስርአትና የሚያስቀምጡላቸው መመሪያ የህፃናትን መልካም ባህሪ ለመቅረፅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች በህፃናት ስነስርአት ላይ ጉልህ አስተዋፅኦ አላቸው።

የህፃናት ስነስርአት እድገት በተለይ የሚመሰረተውና የሚመራው እንደ ምሳሌ አድርገው በሚወስዷቸው ወላጆቻቸው ነው። ህፃናት ከሚሰጣቸው መመሪያ ይልቅ በየእለቱ ከወላጆቻቸው ወይንም ከአሳዳጊዎቻቸው ከሚመለከቱት የንግግርና የተግባር እንቅስቃሴ የተለያየ ስነምግባርን ይማራሉ። እነርሱ እንዳያደርጉ ቢነገራቸውም ነገር ግን ልጆችን አታድርጉ የሚባለውን ነገር ወላጆቻቸው ወይንም አሳዳጊዎቻቸው በተደጋጋሚ የሚፈፅሙት ከሆነ ብዙ ጊዜ ልጆች ያንን ባህርይ ይዘው የማደግ ሁኔታ ይታያል። ይህንን ድርጊት የሚፈፅሙት ወላጆቻቸውን ወይንም አሳዳጊዎቻቸውን ምሳሌ አድርገው በመውሰድ ነው። የህፃናትን መልካም ስነስርአት ለመቅረፅ የወላጆች ምሳሌነት ታላቅ መሳሪያ ነው።

ሐ

አወያይ

አንድ ህፃን ለረዥም ጊዜ የበለጠ ቅርበት ያለው ከወላጆቹ ወይንም ከአሳዳጊው ይልቅ ከእድሜ አቻ ጓደኛ፣ ከጎረቤት፣ ከመምህራን ወይም ከሞግዚት ጋር ነው። ለህፃኑ የበለጠ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ህፃኑ ላይ ተፅእኖ በማሳደር ባህሪውን ወይም ስነ ምግባሩን ለመቅረፅ ሃይል ይኖራቸዋል።

መ)ሌሎች ህፃናት

አወያይ፡

ሌሎች ህፃናት፡- ህፃናት ከህፃናት (ከእኩዮቻቸው) ጋር በተደጋጋሚ በሚኖራቸው ግንኙነት ጠባያቸው ሊለወጥ ወይንም ሊሻሻል ይችላል። ተፅእኖ ማሳደር የሚችሉ ህፃናት ተፅእኖ ማድረግ በማይችሉት ህፃናት ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራሉ።

ሠ) መምህራን

አወያይ

ከመምህራን ተግባራት አንዱ የህፃናትን ስነምግባር መቅረፅ ነው። ስለዚህም መምህራን በአላማ በህፃናት ባህሪ ላይ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ። በትምህርት ገበታ ላይ ካላቸው አስተዋጾ በተጨማሪ ከወላጆችና ከእድሜ አቻዎቻቸው ቀጥሎ ለህፃናት አርአያ የሚሆኑት መምህራን ናቸው።

ረ) መገናኛ ብዙሀን

አወያይ

ህፃናት በቤት ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቴሌቪዥን በመመልከት ወይም ራዲዮ በማዳመጥ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ። በተደጋጋሚ በቴሌቪዥን የሚመለከቱት ወይም በራዲዮ የሚሰሙት ነገር በባህርያቸው ላይ ተፅእኖ ያሳድራል።

## 2. የቅጣትን ምንነት መገንዘብ

1. ህፃናት ስነስርአት ያላቸው እንዲሆኑ ወላጆች የሚጠቀሚቸው ዘዴዎች ምን ምንድን ናቸው?

አወያይ፡ ወላጆች በሚከተሉት  ነጥቦች ዙሪያ ለጥቂት ደቂቃዎች በየግላቸው በጥሞና እንዲያስቡበት ማበረታታት፡-

እስቲ እርስዎ ወይም እርስዎ የሚቀርቧቸው ሰዎች ልጆችን ስነ ስርአት ለማስያዝ የሚያደርጓቸውን ነገሮች ማለትም ልጅዎ ስነስርአት አላከብር ቢል ልጁን ስነስርአት ለማስያዝ የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ለአንድ ደቂቃ አስቧቸው።

በልጅነት ዘመንዎ ቤተሰቦችዎ ልጆችን ስነስርአት ለማስያዝ የተጠቀሟቸው ዘዴዎች ምን ምን እንደነበሩ እስቲ ለአንድ ደቂቃ ያስቡበት ማለትም እርስዎ ልጅ በነበሩበት ወቅት፤ ልጆች ስነስርአት አላከብር ቢሉ ወይም ስነስርአት ቢጥሱ ወላጆችዎ ልጆችን ስነስርአት ለማስያዝ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችን በተመለከተ

ተሳታፊዎች በየግላቸው በጥሞና ለሁለት ደቂቃ እንዲያስቡ ከተደረገ በኋላ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማበረታታት። ተሳታፊዎች ምንም ነገር ሳይደብቁ ወይም “ይሄን አልናገርም” የሚል አቋም ሳይዙ በተቻለ መጠን በባህሉ የሚደረጉትን በግልፅ እንዲያቀርቡ ማበረታታት። ለከተሳታፊዎች የሚሰጡትን መልሶች በሙሉ በጥቁር ሰሌዳው ወይም በተለጠፈው ትልቅ ወረቀት ላይ ይመዝግቡ።

ትርጉም እና ማብራሪያ

አንዳንድ ጊዜ ህፃናት ወላጆቻቸው እንዲኖራቸው ከሚሹት ስነ ምግባር ያፈነግጣሉ። በዚህን ጊዜ ወላጆች የማረሚያ እርምጃ ይወስዳሉ። የህፃናትን የተሳሳተ ስነ ምግባር ለማረም የሚወሰደው እርምጃ ከባህል ባህል

፣ ከወላጅ ወላጅ ወይንም ከአሳዳጊ አሳዳጊ ይለያያል። በባህላችን በተለምዶ ስነስርአት ማስያዝ ማለት ቅጣት ተብሎ ይወሰዳል። ስነስርአትን ዘወትር የሚጥስ ልጅም ‹ያልተቆነጠጠ› ይባላል። በተለምዶ ‹ሴት ያሳደገው› ሚል ስያሜ ለአንድ ልጅ የሚሰጠው እየደበደበ ስነስርአት የሚያስይዘው (የሚቀጣው) አባት በቤቱ ሳይኖር ሲቀር መሆኑ ይታወቃል፡፡

## **2.1.** የቅጣት እና የአወንታዊ ስርዓት ማስያዝ ልዩነት

ከላይ እንደተገለጸው አብዛኛው ሁብረተሰብ ሥርዓት ማስያዝ ማለትን ከቅጣት ጋር ያያይዘዋል። የሥርዓት ማስጠበቂያ ዋና ስልት ቅጣት እንደ ሆነ አድርገውም ይቆጥሩታል።

ይህ ሁኔታ በተወሰነ መልኩ ክፉና ደጉን ለይተው ለሚያውቁ አዋቂዎች፤ ማለትም እያወቁ ሆን ብለው ወይም በቸልተኛነት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ በማይወጡ አዋቂዎች ብቻ ሊሰራ ይችላል።

አወያይ ፦ ክፉና ደጉን ለይተው ማወቅ በማይችሉ ህጻናት ላይ ስርአት ማስያዝን ከቅጣት ጋር ማገናኘት ጠቃሚ አይደለም። ምክንያቱም ህጻናትን ስንቀጣቸው (በአካላዊ ቅጣትም ሆነ በስሜት ጎጂ ቅጣት) እነሱ የሚሰማቸው ለህመም መዳረጋቸው እንጂ ግዴታቸውን ከመወጣት ጋር ሊያገናዝቡትም ሆነ ወላጅ ቅጣትን ከስርአት ጋር ያጣመረበትን ቅን ምክንያት እንዲገባቸው ችሎታቸው አይፈቅድም።

## **2.2.** ቅጣት ምንድነው**?**

ሰዎች ህግን ጥሰው/ደንብ ተላልፈው/ ሲገኙና ያልተገባ ፀባይ ሲያሳዩ ጥፋት ሆኖ ስለሚታሰብ ለጥፋታቸው የሚወሰደው እርምጃ ቅጣት ይባላል። የእንደዚህ ዓይነቱ ቅጣት ዓላማም ህግና ደንብን የተላለፉ ሰዎችን በመጉዳት በአሉታዊ መንገድ የሰዎችን ባህርይ መቆጣጠር ነው።

አወያይ፡- ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ቅጣትን በመፍራት ከጥፋት እንዲቆጠቡ ህጎችና ደንቦች የተለያዩ የቅጣት ስልቶችን ያስቀምጣሉ። ይህም እንኳ ሆኖ ቅጣት ብዙውን ጊዜ አዋቂዎች ከማይፈለግ ድርጊት እንዲታቀቡ ቢያደርግ እንጂ የሚፈለገውን ባህርይ እንዲለምዱ ሲያደርግ አይታይም።

## 2.3. ቅጣት ከህጻናት አንጻር ሲታይ

‹ህጻናት ስነስርአት ያላቸው እንዲሆኑ መጀመሪያ መቀጣት(መጎዳት) አለባቸው። የሚለው ጎጂ አመለካከት ነው። የሚያሳዝነው ግን ይህ አመለካከት በህብረተሰባች በስፋት ይስተዋላል። በተጨባጭ የተረጋገጠው ነገር ግን ከዚህ አመለካከት በተቃራኒው ሲሆን ይኸውም ህጻናት መልካም ስሜት ሲሰማቸው በሁሉም አቅጣጫ የተሻለ ውጤታማ እንደሚሆኑ የተረጋገጠ ነው፡

## 2.4. የቅጣት አይነቶች

በተለምዶ ህጻናት ላይ የሚተገበሩ ቅጣቶች በዋናነት ሁለት ዓይነት ናቸው።

1. አንዱ አይነት ቅጣት ስሜትን ክፉኛ የሚጎዳ ዘለፋ/ ነቀፋ ወይም ስድብን የያዘ ቅጣት ነው።

- ቀጭን ትዕዛዝ
- የሚጎዱ አባባሎች
- ከልካይ ትዕዛዞች
- ማስፈራሪያ አባባሎች
- አንቋሻሽ/ሞራል ሰባሪ አባባሎች

2. ሁለተኛው አካልን እና

ስሜትን የሚጎዳ ቅጣት ነው።

- መምታት
- ሥራ ማሰራት
- ማንበርከክ
- ምግብ መከልከል
- ማሰር
- ማቃጠል
- በርበሬ ማጠን

አወያይ፡-እባክዎትን የቅጣት አይነቶችን ያብራሩላቸው

ቀጭን ትዕዛዝ ወይንም ስሜት የሚጎዱ አባባሎች፤ምሣሌ፣“ዝም ብለህ ቁጭ በል!” “መቶ ጊዜ ደጋግመህ ጻፍ!” “ባንተ ጊዜዬን አላባክንም!”

ከልካይ ትዕዛዞች፡-"እንደዚህ ታድርግ!"

ማስፈራሪያ አባባሎች፡-“ወሬህን የማታቆም ከሆነ ወስጄ ጫካ እጥልሀለሁ።”

አንቋሻሽ/ሞራል ሰባሪ አባባሎች፡-

"እንደ ወንድምህ ለመጻፍ ያልታደልክ ነህ?" “ደንቆሮ ነህ!” “ምን ጊዜም የማይገባህ ደደብ ነህ!”“እንዳንተ አይነት ከሚወለድ ቢቀር ይሻላል!”

- አሰልቺ ተግባራትን ማሰፈፀም ለምሳሌ አንድ ጆግ ውሃ ጠጣ

 ቅጣት (ልጅን በአካልና በስሜት መጉዳት) ስነሥርዓት የማስተማሪያ ዘዴ አይደለም!

አወያይ

ህጻናት ያሉበት የአእምሮ ብስለት ደረጃ እንደአዋቂዎች ለማገናዘብ ስለማያስችላቸው ፤ እንዲሁም በአብዛኛው ስሜታቸውን የመቆጣጠር ችሎታን ስላላዳበሩ ስነስርአት ለማጉደል የመጋለጥ እድላቸው ሰፊ ነው። በመሆኑም እነኚህን የግንዛቤ ችሎታቸው ገና በማደግ ላይ ያሉ ዜጎች በማስተማር እንጂ በመቅጣት ስነስርአት ለማስያዝ መሞከር ለግለሰብም ይሁን ለሀገር ጉዳት አለው ። አሉታዊ ቅጣት በግለሰቡና በማህበረሰቡ ላይ ችግር የሚፈጥሩ ዜጎች እነደሚፈጥር ለተሳታፊዎች ይንገሩዋቸው።

## 2.5. ህጻናትን መቅጣት የሚያስከትላቸው ችግሮች

- ሕፃናት ከቅጣት ሊገነዘቡ የሚችሉት የማንፈልገውን ነገር ለማስቆም ሰውን መጉዳት ተቀባይነት ያለው መሆኑን ነው።
- ቅጣት ልጆች በትምህርት ቤቶች ውስጥ ነውጠኛና በጥባጭ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።
- ቅጣት ብዙ ልጆችን ፈሪና በራሳቸው የማይተማመኑ ሲያደርጋቸው አንዳንዶችን ደግሞ ተጋፊና ጉልበተኛ/ የሌሎችን መብት የሚጥሱ እንዲሆኑ ሲያደርጋቸው ይታያል።
- የሚያድጉ ህጻናት ቂመኛ ይሆናሉ። ለወንጀል፣ ለጭንቀትና ለጠብ አጫሪነት መጨመር፣ ለነፃነት ማጣትና ለሌሎች ግድ አለመኖር ለመሳሰሉ ባሕርያት
- ቅጣት ከባድ የሆነ ስነ ልቡናዊ እና አካለዊ ጉዳት ያመጣል

## **2.6.** የህፃናት ቅጣት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ አካላዊና አእምሯዊ የህፃናት ቅጣት በስፋት የተለመደ ነው። ይህ አሉታዊ የሆነ ግድፈትን የማረሚያ መንገድ ህፃናትን ስነ ምግባር የማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነ በብዙ ሰዎች ይታሰባል። መንግስት በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪን ስነስርአት ለማስያዝ አካላዊ ቅጣት ህገወጥ መሆኑን ደንግጎ እንኳ በርካታ ትምህርት ቤቶች ቅታትን ለልጆች ስነ ምግባር የማስተማሪያ መንገድ አድርገው እየተጠቀሙበት ይገኛል።

ቅጣት ልጆችን ስርአት ማስያዣ ሆኖ ሊስፋፋ የቻለው በሚከተሉት አበይት ምክንያቶች ነው

**1.** ልማድ

> አወያይ
>
> ልማድ፡-ብዙ ጎልማሶች አካላዊና አእምሮአዊ ቅጣት ህፃናትን ስነምግባር ለማስተማር ውጤታማና ተቀባይነት ያለው ዘዴ እንደሆነያስባሉ። ነገር ግን ቅጣቱ ከላይ  እንደተገለፀው በህፃናት የወደፊት ህይወት ላይ እንዲሁም በማህበረሰቡ ላይ ጉዳት ሲያደርስ ይስተዋላል፡

**2.** አማራጭ የማረሚያ መንገድ ስለመኖሩ የግንዛቤ ችግር

> አወያይ
>
> አማራጭ የማረሚያ መንገዶች መኖራቸውን በተመለከተ የግንዛቤ ችግር መኖር፡-        ብዙ ወላጆች ከአካላዊ ቅጣት ይልቅ የተሻለና ውጤታማ አማራጭ የማረሚያ መንገድ መኖሩን አያውቁም ወይንም ቢያውቁም የአማራጭ ማረሚያ መንገድ ውጤታማነት ላይ እርግጠኛ አይደሉም። በተለይ ብዙዎቻችን በቅጣት እንድናምን የሚያደርገን አሉታዊ ቅጣት ሰዎችን ከጥፋት ለጊዜው ሲያስቆም ስለምናይ ነው። አንድ አታድርግ የተባለውን ነገር በማድረግ ላይ የሚገኝን ህጻን በጥፊ ፤ በልምጭ ወይም [illegible] ጥፋቱን

> አወያይ፡- የወላጅ/የአሳዳጊ ወይም የመምህራን ትዕግሥት ማጣት
>
> አወንታዊ የስነስርአት ማስያዣን መንገድ ለመጠቀም ብዙ ትዕግሥትና ከህፃናቱ ጋር አብሮ ጊዜ ማሳለፍን ይጠይቃል። ህፃናትን በማሳተፍ ስለ ስነስርአት ማስተማር፤ ህፃናት አንዳንዴ ሲያጠፉ አይቶ እንዳላየ ማለፍ ፤ ያልተቋረጠ ክትትል ማድረግ፤ ጥፋት አጥፍተው ሲገኙ ስለጥፋቱ በትዕግስት ማወያየት ወዘተ... እልህ አስጨራሽ ሊሆን ይችላል። በአንፃሩ ቅጣት (አሉታዊ የሆነው የስነስርአት ማስያዣ መንገድ)     ጊዜ አይፈጅም። ከልጁ ጋር በንግግር ጊዜ ከመፍጀት አጥፊውን ልጅ በጥፊ በማለት ወይም በማስመሪያ በመዠለጥ አሳምሞ ዝም ማሰኘትን እንደቀላል አማራጭ  አድርገን እንወስዳለን። ታዲያ ለጊዜው ቀላል አማራጭ አድርገን የወሰድነው እርምጃ ዘላቂ የመንፈስ መረበሽና የባህርይ ችግር መፍጠሩ አይቀርም።

አወያይ

ሰሌዳውን ወደታች በተሰመረ መስመር ለሁለት ይክፈሉት። በመቀጠልም በቀኝ በኩል ባለው ግማሽ በላይኛው ጠርዝ “አወንታዊ ስነ ስርአት ማስያዣ” እንዲሁም በሁለተኛው ክፍል የላይኛው ጫፍ ላይ ደግሞ በግራ በኩል ባለው ግማሽ በላይኛው ጠርዝ ቅጣት ” በማለት ፃፉ። ተሳታፊዎች የእነዚህን ልዩነት እንዲወያዩበት በማድረግ ከታች የተቀመጠውን የማጠቃለያ ሰንጠረዥ ያንብቡላቸው

## **2.7.** በህብረተሰባችን በወላጆችና በመምህራን ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው እና በተለምዶ ቅጣትን የሚያስከትሉ የልጅ ባህርያት

1. አንድ ነገር ለማድረግ/ለማግኘት ፋታ የለሽ ጥያቄ ማቅረብ፤

አወያይ፡-ህጻናት በሁለትና በሦስት ዓመታቸው ስለአንድ ነገር ደጋግመው ቢጠይቁ የተለመደና ጤናማ ነው ተብሎ ይወሰዳል። አራት/አምስት ዓመትና በላይ የሆናቸው ልጆች ግን እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ የመጠየቅ አቀራረብ ካዘወተሩ እንደ ባሕርይ ችግር ተደርጎ ይታያል እንጂ እንደ ጤናማ ባህርይ ሊወሰድ አይችልም።

2.

አወያይ፡-ህጻናት በሌሎች ከነሱ ባነሱና ደከም በሚሉ ህጻናት ላይ የማንቋሸሽና የፀብ አጫሪነት ባህርይ በማሳየት ለድብድብና ለብጥብጥ ሲጋበዙ፤ የራሳቸውንም ሆነ የሌሎችን ወይም የቤትን ንብረት ሲያወድሙ ወይም ሲያበላሹ።

3. አለማዳመጥና ትኩረት አለመስጠት፤

አወያይ፡-ህጻናት በአንድ ነገር ላይ ለረጅም ሰዓት ትኩረት ሰጥቶ መከታተል አይችሉም። በአንዴ ሁሉንም ለማየት ስለሚፈልጉ በአካባቢያቸው የሚሆነውን ነገር ትኩረት ለመስጠት ይቸገራሉ ። ይህ ሁኔታም ለትንንሽ ሕጻናት የተለመደና ጤናማ ድርጊት ነው።

4. ማታለልና መስረቅ፤

አወያይ፡-የራስ ያልሆነን እቃ/ንብረት አጭበርብሮ ወይም ከእይታ ሰውሮ ሲወስድ፤

5. ሌሎችን አለማክበር

አወያይ፡-ማንኛውም ባህል ለሌላው አክብሮትን የሚገልጽበት የራሱ የሆነ መንገድ አለው፡ ለምሳሌ በሀገራችን ካሉ ባህሎች አንዱን ብንጠቅስ፣ አዋቂዎች ሰዎች ሲያወሩ ልጆች ጣልቃ ገብተው ማውራት የለባቸውም። ምክንያቱም ለአዋቂቹ ክብር አለመስጠት ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው፤

6. መነቃቃት አለመቻልና ፍላጎት ማጣት፤

አወያይ፡-አንድ ሕጻን መሥራት/ማከናወን/የሚገባውን ተግባራት ለማከናወን/ለመፈጸም/ መነሳሳትና ፍላጎት የማጣት ባህርይ ሲያሳይ፤ ለምሳሌ፣ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ አለመፈለግ፣

7. ሃላፊነትን አለመወጣት፤

አወያይ፡-በአጸደ ህጻናት እድሜ ደረጃ ካሉ ሕጻናት ጀምሮ ልጆች እንደየእድገት ደረጃቸው በቤት ውስጥ ተሳትፎ ማድረግና ‹እኔም በቤት ውስጥ ድርሻ አለኝ› ብለው እንዲያስቡ ይጠበቃል፡ ይህንን ሳይወጡ ሲቀሩ ግን ተገቢ ያልሆነ ባህርይ እያሳዩ መሆኑን ይገልጻል፡

8. የወላጆችንና የመምህራንን ሃላፊነት መፈታተን (የእምቢተኝነት፤ የተባሉትን የአለማድረግ ዝንባሌ)

አወያይ፡-የሁለትና የሦስት ዓመት እድሜ ላይ ያሉ ህጻናት የወላጆቻቸውንና የመምህራኖቻቸውን ኃላፊነት የመፈታተን ባህርይ ቢያሳዩ የሚጠበቅ የእድገት ሂደት ሆኖ የሚወሰድ ሲሆን በእድሜ ከዚያ በላይ የሆኑ ህጻናት ተመሳሳይ ባሕሪ ካሳዩ ግን ሥርዓት ማጣት ተደርጎ ይወሰዳል።

9. ኃይለ ቃል መጠቀም/በቁጣ በመጮህ መናገር፤

አወያይ፡-ሕጻናት አብዛኛውን ጊዜ ይህን የሚማሩት ከአዋቂዎች ነው። የአዋቂዎችን ቀድተው በማስመሰል ሲተገብሩ፡ ልጆቹን ከመቅጣት ይህን ዓይነት ባህርይከየት እንዳገኙት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

10. ያለ ምንም በቂ ምክንያት በተደጋጋሚ የቤት ሥራን አለመሥራት፤ በፈተና መውደቅ

11. ከክፍል መቅረት፣ ወደ ክፍል ለመሄድ ፍላጎት ማጣት

አወያይ፡-ወላጆች ሳያውቁትና ሳይፈቅዱ ያለ ተጨባጭ ምክንያት ከትምህርት ቤት የመቅረት ልማድ እየጨመረ መምጣት

አወያይ፡-

ሕጻናት በሚሰሩት ሁሉ የአዋቂዎችን ሥራ ይኮርጃሉ። ስለዚህ ልጅ በተወሰነ ደረጃ ያልተገባ ባህርይ የሚያሳይ/የምታሳይ/ ከሆነ የወላጅን ወይም ሌላ ግለሰብን አርአያነት ተከትሎ/ተከትላ መሆን አለመሆኑን ወላጅ ማረጋገጥ እንዳለበት ለተሳታፊዎች ያስረዱ።

## 2.8. ስነሥርዓት እና የቅጣት ልዩነቶች ማጠቃለያ ለወላጆች/አሳዳጊዎች

| አዎንታዊ ስነስርአት ማስያዝ | ቅጣት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| ተገቢ የሆነ ባህርይን ማስተማር ፤ ማሰልጠን ማለት ነው። | የማይፈለግ ባህርይን ለማስተው ሆን ብሎ ስቃይ/ህመም እንዲሰማው ማድረግ |
| ትኩረት የሚያደርገው ሕፃናት እንዲሠሩት በምንፈልገው ላይ ነው | ትኩረትየሚያደርገውሕፃናትእንዳይሠሩት በምንፈልገው ላይ ነው፡ |
| የኃላፊነት ስሜት ከራስ እንዲመነጭ ያደርጋል | ህጻናትን በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል |
| የህጻናት ባህርይ በቀጣይነት እንዲሻሻል ያደርጋል | የጥረትንና የተነሳሽነትን ባህርይ ያዳክማል |
| ህጻናት የዘላቂ ክህሎት ባለቤት እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል | ተገቢ ያልሆነ ባህርይን የሚገታው ለጊዜው ነው |
| በአዋቂዎችና በህፃናት መካከል ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል | በህፃናትና በአዋቂዎች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲቋረጥና የስሜት መራራቅ/ ክፍተት እንዲኖር መንስኤ ይሆናል። |
| የተለያዩ ባሕርያት የሰው ተፈጥሮአዊ ገጽታ መሆናቸውን ተቀብሎ ስሜታዊ ብቃትን መጠበቅንና ራስን መቆጣጠርን ያስተምራል | ህጻናትን ያሸማቅቃል፤ ስሜታቸውንም በሌሎች ላይ በቁጣ እንዲገልጹት ያደርጋቸዋል |
| ህጻናት በትምህርት ቤት የተሳካላቸው እንዲሆኑ ክህሎቶችን ያስተምራል | ህጻናት ትምህርት ቤት ለነሱ ምቹ ቦታ እንዳልሆነ አድርገው እንዲያስቡት ያደርጋቸዋል |
| ህጻናት በሕይወት ጎዳና እንዴት ስኬታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ በተመለከተ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል (መንገዱን ያሳያቸዋል). | ውድቀትና ስኬታማ አለመሆንን እንዲያስቡ ያደርጋል |
| ህጻናት ከውድቀታቸው የሚማሩ፣ በሚሠሩት ሥራ አስፈላጊነት ሚተማመኑ፣ ሌሎችን ለማገዝ ግድ የሚላቸው እንዲሆኑ ያደርጋል፤ እንዲህ ዓይነት ባህርይ ያላቸው ህጻናት ይህን ስሜታቸውን ሌሎችም እንዲጋሩት ያደርጋሉ | ህጻናት ራሳቸውን እንዲጠራጠሩ፤ ሃፍረት እንዲሰማቸውና እንዲሸማቀቁ መንስኤ ይሆናል። እንደዚህ ዓይነት ስሜቶችንም በውስጣቸው አምቀው እንዲይዙ ያደርጋቸዋል። |
| ህጻናት ወደ ትብብር የሚያድግ የኃላፊነትና የተፈላጊነት ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋል | ህጻናት ለትብብር ቦታ ማይሰጡትን እንደ ቁጣና ብቀላ ያሉ መጥፎ ባህርያት በውስጣቸው ይዘው እንዲያድጉ መንስኤ ይሆናል |
| ህጻናት ከአዋቂዎች ባዩት መልከም ነገር መሠረት ራሳቸውን ለማነጽ እንዲነሳሱ ያደርጋቸዋል | ህጻናት (ያዩትን) ሆኖ የመገኘት ሳይሆን የማስመሰልን ፍላጎት እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል |

## 3. አሉታዊና አወንታዊ ስነስርአት ማስያዣ መንገዶች

ስነስርአት ማስያዣ መንገዶች አወንታዊ እና አሉታዊ ተብለው ይፈረጃሉ።

### 3.1. አሉታዊ የስነስርአት ማስያዣ መንገዶች

አሉታዊ የስነ ስርአት ግድፈትን የማረሚያ መንገድ መገለጫው ህፃናት ተገቢ ያልሆነ ስነ ምግባር እንዳያሳዩ ወይንም ደግመው እንዳይፈፅሙ በሚል ህጻናቱን በአካል ወይም በስሜት ወይንም በአንድ ጊዜ በሁለቱም አይነት ዘዴዎች መጉዳት ነው።

አወያይ

ይህ ዘዴ አካላዊ፣ ስሜታዊ ወይንም ሁለቱንም አይነት ጉዳት ያደርሳል። ይሁን እንጂ ህፃናት ከቅጣቱ በኋላ የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣታቸው ማረጋገጫ አይሰጥም። ህፃናት ጥፋት የማይፈፅሙት የሚደርስባቸውን ቅጣት በመፍራት እንጂ በፍላጎትና በፈቃደኝነት አይደለም። በብዙ አጋጣሚዎች አሉታዊ የግድፈት ማረሚያን ተከትሎ ህፃናት ጤናማ ያልሆኑ ባህርያትን ያዳብራሉ።

የሚከተሉት አሉታዊ የስነ ስርአት ግድፈትን የማረሚያ መንገዶች በኢትዮጵያ በስፋት ይታያሉ፡

የአእምሮ ጉዳት የሚያደርሱ የማረሚያ መንገዶች ምሳሌዎች፡-

- ህፃናትን መስደብ ወይንም በመጥፎ ቅፅል ስም መጥራት
- ህፃናትን የማይረቡ ወይንም ከሌሎች ህፃናት የሚያንሱ እንደሆኑ መተቸት
- ህፃናት ሲያናግሩ መልስ መንፈግ ወይም የሚጠይቁትን ነገር ለረጅም ጊዜ ችላ ማለት
- ህፃናት ለረጅም ጊዜ በአስፈሪ ሁኔታ ውስጥ ብቻቸውን መተው(ለምሳሌ፡- በጨለማ ክፍል ፣በምሽት ከቤት በማስወጣት)

አካላዊና አእምሯዊ ጉዳት የሚያደርሱ አሉታዊ የማረሚያ መንገዶች ምሳሌዎች፡-

- በህፃናት ላይ የተለያዩ አካላዊ ጉዳት ማድረስ (የህፃናትን መቀመጫ በእጅ መምታት ፣ጥፊ ፣ቁንጥጫ ፣ኩርኩምና በአለንጋ መግረፍ)
- በሚቆረቁር ቦታ በማንበርከክ መጉዳት
- የተለያየ አድካሚ የአካል እንቅስቃሴ በማሰራት ማድከም
- ምግብ በመከልከል በረሃብ እንዲጎዱ ማድረግ

አወንታዊ ያልሆኑ ዘዴዎች ለጊዜው ውጤታማ ቢመስሉም በዘላቂነት ግን ብዙ ጉዳቶችን ያስከትላሉ። እነዚህም የቅጣት ዘዴዎች ህፃናቱ እንዲተውት ከሚፈለገው ድርጊት ለተወሰነ ጊዜ እንዲርቁ ያደርጋቸዋል እንጂ በኋላ ተመልሰው ያንን ድርጊት ሲፈፅሙት ይስተዋላል፡

አወያይ

በጎጂነታቸው (በቀጪነታቸው) የሚፈሯቸው ሰዎች በአካባቢው እስካሉ ብቻ ህፃናቱ ተገቢ ያልሆኑ ተግባራትን ከመፈፀም ይታቀባሉ። የሚፈሩት ጎጂ (ቀጪ/ተማቺ) ሰው ከአካባቢው ዘወር ሲል ግን አላስፈላጊውን ባህርይ ይፈፅሙታል።

ልጆችን አካልንና አእምሮን ጎጂ በሆኑ ቅጣቶች ስነስርአት ማስያዝ ወደፊት በግለሰቡና በማህበረሰቡ ላይ ችግር የሚፈጥር መሆኑ በተለያዩ አካባቢዎች ታይቷል።

አወያይ

- በአሉታዊ የማረሚያ ዘዴ ያደጉ ሰዎች ተሸማቃቂና በራስ መተማመን የሌላቸው ሆነው ታይተዋል። በሌላ በኩል በዚህ አይነት የቅጣት ዘዴ ያደጉ ሰዎች ከሌሎች ጋር በማይግባቡበት ወቅት ሀይልን መፍትሄ ለማድረግ የሚቸኩሉ ሲሆኑ ይታያል።
- ለህፃናት መጥፎ ባህርይ በመንስኤነት ከሚጠቀሱት ችግሮች መካከል አሉታዊ የህፃናት ስነስርአት ማስያዣ መንገድ አንዱ ነው።

## 3.2. አወንታዊ የስነስርአት ማስያዣ መንገዶች

አወንታዊ የሆነ ስነስርአት ማስያዣ ዘዴ ገና ከጠዋቱ ህፃናት ስነስርአትን እንዲማሩ በፍቅር ማወያየትን ያካትታል።

አወንታዊ የስነስርአት ማስያዣ ዘዴዎች ህፃናት ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያርሙ የሚያግዙ ዘዴዎች ሲሆኑ አሉታዊ የስነስርአት ማስያዣ ዘዴዎች ግን በፍላጎት ራስን ለማረም ወይንም አስፈላጊ ስነ ምግባርን በፍላጎት በታዳጊው ውስጥ ለማስረፅ አይጠቅሙም። ስለዚህ ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ህፃናትን ለማረም ውጤታማ የማረሚያ መንገዶችን ለይተው ማወቅና መጠቀም ይኖርባቸዋል።

አወንታዊ የስነ ስርአት ማስያዣ መንገዶች አላማ አላቸው። አላማውም ህፃናትን በአካላዊ ወይንም በአእምሮአዊ ቅጣት ህመም ሳይደርስባቸው የስነ ስርአትን አስፈላጊነት እንዲገነዘቡና ስነስርአትን እንዲያከብሩ ማድረግ ነው።

አወያይ

አወንታዊ የስነ ስርአት ማስያዣ መንገዶችን የሚጠቀሙ ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ምን ምን ዘዴን እንደ ሚጠቀሙ ተሳታፊዎችን ይጠይቋቸው እና መልሱን በሰሌዳ ላይ ይፃፉ። ከዚያም ተሳታፊዎች የሰጡትን መልስ ከታች ከተገለፀው ማብራሪያ ጋር እያገናዘቡ ያስረዱዋቸው።

አወንታዊ የስነ ስርአት ማስያዣ መንገዶችን የሚጠቀሙ ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ያደርጋሉ፡-

- ከህፃናቱ ጋር ስለ ስነስርአት ምንነትና ስነስርአትን ያለማክበር ስለሚያስከትለው ጉዳት ይወያያሉ።
- የቤተሰብ አባላትን (ህፃናትን ጨምሮ) ያከብራሉ ፤ያፈቅራሉ።
- የህፃናቱን ውሎና አዳር በቅርበት ይከታተላሉ። ህጻናቱ የት እንደዋሉ፤ ከማን ጋር ምን ሲደርጉ እንደዋሉ፤ ምን ጥሩ ነገርና ምን ችግር አጋጥሟቸው እንደዋለ ይከታተላሉ።
- ከልጆቻቸው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ልጆችና አዋቂዎች ባህርይ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ይህን በማድረግም በባህርያቸው ችግር ያለባቸው ሌሎች ልጆችና አዋቂዎች የልጃቸውን ባህርይ በማይፈለግ መንገድ እንዳይመሩት የመከላከል እርምጃ ይወስዳሉ።
- ወላጆች ራሳቸው ስነስርአት በማክበር ለልጆች ይህንን ባህርይን በተግባር ያስተምራሉ። ይህ ሲሆን ልጆች ከወላጅ በሚሰሙት ብቻ ሳይሆን ይበልጥ አስተማሪ በሆነው የወላጅ ተግባር/ባህርይ ራሳቸውን ይቀርፃሉ።
- ስነስርአት የማያከብር የቤተሰብ አባል ላይ ምን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ከህፃናቱ ጋር ይወስናሉ። በዚህ መንገድ ወላጆች ህፃናቱን ህግ በማውጣትና ገደብ በማስቀመጥ ሂደት እያሳተፉ ክብር እንዲሰማቸው ያደርጋሉ። ይህ አወንታዊ የስነ ስርአት ግድፈትን የማረሚያ ዘዴ ህፃናት በጥፋታቸው የሚወሰድባቸውን እርምጃ ከወዲሁ እንዲያውቁትና ሲሆን ከጥፋት እንዲቆጠቡ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ የሚወሰድባቸውን እርምጃ በፈቃደኝነት እንዲቀበሉ እንዲሁም ለተፈፀመው ጥፋት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ በእውቀትና በሃላፊነት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል።
- በአወንታዊ የስነስርአት ግድፈትን የማረሚያ መንገድ ወላጆች የልጆቻቸውን ምርጫ ያከብራሉ። ነገር ግን ህፃናት ተገቢውን ስነምግባር እንዲላበሱ መመሪያ ይሰጣሉ፤ ያለማቋረጥ ክትትል ያደርጋሉ።

 አወንታዊ የስነስርአት ግድፈትን የማረሚያ መንገድ ውጤታማ የሚሆነው ህፃናቱ በወላጆቻቸው ፍቅር ስለሚሰጣቸውና ባለማቋረጥ ተገቢ አመራርና ክትትል ስለሚደረግላቸው ነው።

አወያይ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ወላጆች በሚከተሉት ሁለት ነጥቦች ዙሪያ ለደቂቃዎች በጥሞና እንዲያስቡ ያበረታቷቸው፡-

ልጆችዎን ስርአት ለማስያዝ የሚያደርጓቸውን ነገሮች እስቲ አስቧቸው።

በልጅነት ዘመናችሁ ቤተሰቦቻችሁና ጎረቤቶቻችሁ እናንተን ስርአት ለማስያዝ ይጠቀሙባቸው የነበሩት መንገዶች ምን ምን ነበሩ?

ሁሉም ተሳታፊዎች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማበረታታት። እንዲሁም ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥያቄዎች የሚሰጧቸውን ምላሾች በተዘጋጀው ወረቀት ላይ እንደየምድቡ ያስፍሩ።

አወያይ

የሚከለተሉትን የመልካም ወላጅ መገለጫዎች (ህጻን ልጁ ስነስርአት እንዲኖረው የሚተጋ ወላጅ) ሊተገብር የሚገባቸውን ነጥቦች ይጠቁሟቸው

“ከልጆቼ ጋር ያለኝ ግንኙነት መልካም ነውን?” ብሎ ራሱን ይጠይቃል። ከልጆቹ ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ወላጅ በየእለቱ ከህፃናቱ ጋር የሚያሳልፈው ጊዜ ይኖረዋል። በእነዚህ ጊዜያት ወላጅ ከልጆቹ ጋር እንደየእድሜያቸው አብሮ በመጫወት ወይም በመወያየት ወይም ህፃናቱን በሚያስደስት ተግባር በአብሮነት ጊዜውን ያሳልፋል።

“በባህርዬ ለልጆቼ መልካም አርአያ ነኝን?” በማለት ራሱን ይጠይቃል

ልጆቹን ስነስርአት ለማስያዝ በቅጣት ሳይሆን በማስተማርና ቀጣይነት ባለው ክትትል አስፈላጊነት ያምናል።

## **3.3.** ተግባራዊልምምድ

አወያይ

ተሳታፊዎች ቀጥሎ የሚቀርቡት ታሪኮችን በማዳመጥ በአማራጭነት ከቀረቡት ውስጥ አወንታዊ የሆነውን እንዲመርጡ ያድርጉ። የሚሰጧቸው መልሶች ከምክንያት ጋር መቅረብ ይኖርባቸዋል

**የመጀመሪያ ታሪክ**

**የሰባት አመቷ አስቴር ምሳዋን በጥድፊያ በልታ ለጨዋታ ሮጣ ወጣች። የአስቴር እናት ወደ ቤት ስትገባ የምግብ ፍርፋሪዎች በየቦታው ተዝረክርከው ተመለከተች። የአስቴር እናት እንደዚህ ያለ ነገር ፈፅሞ አትወድም። ከዚህ ቀደም ለአስቴር የተመገበችበትን እቃ ማንሳት፣ የምግብ ጠረጴዛውን ማፅዳትና የወዳደቁ የምግብ ፍርፋሪዎችንም መጥረግ እንዳለባት አበክራ ነግራት ነበር።**

የአስቴር እናት ከሚከተሉት የትኛውን አማራጭ ብትጠቀም አወንታዊ ይሆናል?

ሀ. “አንቺ ሁልጊዜ ዝርክርክ ነሽ። ምግብ ከበላሽ በኋላ ጠረጴዛውን እንኳን ለማፅዳት ግድ የሌለሽ። ትንሹ ወንድምሽ እኮ ከአንቺ ይሻላል።” በማለት አስቴርን በንዴት መናገር።

ለ. “አስቴር አንቺ ግዴለሽ ነሽ። ከዛሬ ጀምሮ ጠረጴዛው ላይ አትመገቢም።” ማለት።

ሐ. የአስቴርን እጅ ለቀም አድርጋ ይዛ እየቆነጠጠቻት “ምግብ ከበላሽ በኋላ ጠረጴዛውን አፅጂ ብዬ ነግሬሽ አልነበረም? ይህን ደግመሽ ታደርጊያለሽ? ለምን ስነ ስርአት አይኖርሽም?”ማለት።

መ. “[illegible]

እ[illegible] ባማለት

መ[illegible]

ሁለተኛ ታሪክ

ሽምሱ የስድስት አመት ልጅ ነው። አንድ ቀን የሽምሱ አባት ልጃቸው በር ላይ ቆሞ መንገደኛን ሲሳደብ ሰሙት። የሽምሱ አባት በልጃቸው ፀያፍ አነጋገር በጣም አዘኑ። ሽምሱ በተደጋጋሚ እንዲህ ያለ ብልግና እንዳይሰራ ተነግሮት ነበር። ከዚህ ቀደምም ሽምሱ ጎረቤት ተሳድቦ ስሞታ ተነግሯል። የሽምሱ አባትም የዚያን ጊዜ በጣም አስጠንቅቀውት ነበር። ከዚህ በኋላ እንዲህ ያለ ነገር ቢያደርግ ከባድ እርምጃ እንደሚወስዱበት ነግረውት ነበር። ስለዚህም አባትየው ሽምሱ ብልግናውን ማቆም ባለመቻሉ በሚፈቀድለት የጨዋታ ጊዜ ላይ ማእቀብ ሊያደርጉበት ወሰኑ።

የሽምሱ አባት ከሚከተሉት እርምጃዎች የትኛውን ቢተገብሩ ነው አወንታዊ ስነስርአት ማስያዝ የሚሆነው?

ሀ. እስኪመሽ ድረስ ጠብቀው ሁሉም የቤተሰብ አባላት በተሰበሰቡበት ሽምሱን መግረፍ

ለ. ሽምሱን ቤታቸው ፊት ለፊት ባላ ኮረኮንች መንገድ ላይ ለሰላሳ ደቂቃ አንበርክከውት ከዚህ በኋላ የሚደግመው ከሆነ ሰላሳ ጊዜ እንደሚገርፉት ማስጠንቀቅ

ሐ. ሽምሱን በመጥራት አሁን ስላደረገው ነገርና ይህን አይነት ጠባይ በተደጋጋሚ በማሳየቱ አባትው በጣም መከፋታቸውን መንገር። በመቀጠልም ጥፋቱ ተደጋጋሚ በመሆኑ ራሱን እንዲያስተካክል እርምጃ እንደሚያስፈልግ መንገር፡ "ሽምሱ አሁን ስትሳደብ ሰምቼህ በጣም አዘንኩ። ሁለተኛ እንዲህ እንዳታደረግ ባለፈው የጎረቤት ሰው ከተሳደብክ በኋላ ተነጋግረናል። ስለዚህም ነገ ቅዳሜ ወንድሞችህ ለኳስ ጨዋታ ፕሮግራም ወደ ሜዳ ሲሄዱ አንተ ከነሱ ጋር ሄደህ በመጫወት ፈንታ እቤት ትቆያለህ። ታዲያ እቤት ብቻህን ሆነህ የምትሳደባቸው መጥፎ ስድቦች ሰውን እንደሚጎዱ እና ይህን መጥፎ ጠባይህን ስለማስተካከል በደንብ አስብበት።"

መ. ለሽምሱ እናት ምሳውን እንዳይሰጡት ትእዛዝ ማስተላለፍ።

ሶስተኛ ታሪክ

የሰባት አመቱ ኮሬ ምክንያቱ ባልታወቀ ጉዳይ በጣም ተናዶ ወደ ቤቱ መጣ። ታላቅ እህቱ በተደጋጋሚ ለማባበል ብትሞክርም ባለመፈለግ በእምቢታ ከቤት ወጥቶ ወደ ጓሮ ሄደ። አሁንም እህቱ ሻይ ይዛለት ሄዳ ለማባበል ሞከረች። ሆኖም ግን ኮሬ የሻይ ብርጭቆውን በንዴት ተቀብሎ ወርውሮ ከሰከሰው። ይህ ሲሆን እናቱ ትመለከት ነበር። ታላቅ እህቱ በጣም ደንግጣ "እማማ ምን ትለው ይሆን?" አለች።

የኮሬ

ተዘጋ

ቢጠቀሙ ነው?

ሀ. ኮሬ ከንዴቱ እስኪረጋጋ ድረስ ጠብቀውት ለምን በንዴት እንደተሞላ መጠየቅ፤ያደረገው ነገር ትክክለኛ ስለመሆን ስለአለመሆኑ ማወያየት፣ እንዲሁም ስላደረገው ነገር ምን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት እንዳለበት በጋራ መነጋገር።

ለ. "አንተ አስቸጋሪና አጥፊ ልጅ ነህ፤ እኛ አንፈልግህም!'' በማለት መናገር።

መ. "ታላቅ እህትህ ላይ እንዴት እንዲህ ታደርጋለህ! ስለ እቃዎች ግዴለሽ ነህ። በስንት መከራ ባመጣነው ገንዘብ እንደምንገዛው ታውቃለህ? ቆይ ጠብቅ አባትህ ይመጣልሃል። አርባ ይገርፍልኛል!"

ሠ. "ከዚህ በኋላ ለአንድ ሳምንት ሻይ የሚባል ነገር እዚህ ቤት አታገኝም።''

ተሳታፊዎች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ አስተያየት ሊሰጡ ይገባል። እንዲሁም ስለአወንታዊና አሉታዊ የስነ ስርአት ማስፈኛ መንገዶች በአመቻቹ ማስታወሻ ላይ የቀረቡትን ሀሳቦች በመንተራስ ማስተዋወቅ ተገቢ ነው። ከላይ በተዘረዘሩት የስነ ስርአት ማስፈኛ መንገዶች ውስጥ  አሉታዊ ናቸው የተባሉት በምን ምክንያት እንደሆኑ ማብራራት የስራ ልግል።

አወያይ

ለመጀመሪያው ታሪክ አወንታዊው ዘዴ፡

ሠ. "እስቴር እስቲ ነይና ጠረጴዛውንና ወለሉን ተመልከቺ። በአንቺ የምግብ ፍርፋሪዎች እንዴት  እንደተበላሸ ተመልከቺ። ባለፈው እንደተነጋገርነው  ጠረጴዛውንና ወለሉን እንድታፀጂ እፈልጋለሁ።"በማለት መንገር።

ሰው ከተሳደብክ በኋላ ተነጋግረናል። ስለዚህም ነገ ቅዳሜ ወንድሞችህ ለኳስ ጨዋታ ፕሮግራም ወደ ሜዳ ሲሄዱ አንተ ከነሱ ጋር ሄደህ በመጫወት ፋንታ እቤት ትቀያለህ። ታዲያ እቤት ብቻህን ሆነህ የምትሳደባቸው መጥፎ ስድቦች ሰውን እንደሚጎዱ እና ይህን መጥፎ ጠባይህን ስለማስተካከል በደንብ አስብበት።"

ለሶስተኛው ታሪክ አወንታዊው ዘዴ፡

ሀ. ኮሬ ከንዴቱ እስኪረጋጋ ድረስ ጠብቀውት ለምን በንዴት እንደተሞላ መጠየቅ፤ያደረገው ነገር ትክክለኛ ስለመሆን ስለአለመሆኑ ማወያየት፣ እንዲሁም ስላደረገው ነገር ምን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት እንዳለበት በጋራ መነጋገር።

በአዎንታዊ  መንገድ ሥርዓትን ማስተማር  የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት

በመጀመሪያ አዎንታዊ ሥርዓት የሕጻናትን በራስ የመተማመን ስሜትን ያዳብራል፤ የዕድሜ ልክ የመማር ፍቅር እንዲኖራቸው እንደሚያደርግም መገንዘቡ አስፈላጊ ነው።

ይኸውም፡-

በአዎንታዊ  መንገድ ሥርዓትን ማስተማር ህጻናት አንድን ነገር በሙሉ ፍላጎትና ቁርጠኝነት እንዲያከናውኑ፤

ሀ) ያነሳሣል፤

ለ/ ያበረታታል፤

ሐ/ ይደግፋል፤

መ/ ሕጻናት ለትምህርት የሚኖራቸውን ፍቅር  ያሳድጋል፤

ሠ/ ራስን በጥሩ ስነ-ሥርዓት ለመግራት ይረዳል፤

ረ/ ብቃትንና በራስ የመተማመን ስሜትን ያጎለብታል።

## 4. ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ሕፃናትን እንዴት በአዎንታዊ መንገድ ስነስርአት ማስተማር ይችላሉ?

ህፃናትን ስነምግባር ለማስተማር በርካታ አወንታዊ መንገዶች አሉ።ህፃናትን ስነምግባር ለማስተማር እድሜያቸውንና አእምሮአዊ እድገታቸውን ከግንዛቤ ማስገባት በጣም ወሳኝ ነው።ህፃናት ስነምግባራቸው የሚያስከትለውን ውጤት ለመረዳት በጣም ብስለት ያንሳቸዋል።የሚከተሉት የስነምግባር ማስተማሪያ ዘዴዎች ለጥቆማ ያህል ቀርበዋል።

1. ሀሳብን ማስለወጥ፡ በአደገኛ ወይም ጉዳት በሚያደርሱ ነገሮች የሚጫወቱ ትናንሽ ህፃናትን ወይንም የሚጣሉ ህፃናትን ትኩረታቸውን ሊለውጥ የሚችል መጫወቻ በመስጠት ወይንም ሌላ ነገር በማሳየት የጀመሩትን ነገር ማቋረጥ ይቻላል። ተለቅ ካሉ ህጻናት ጋር ደግሞ በመወያየት ሃሳብን ማስለወጥ
2. ጥፋትን ችላ ማለት፡-ለጥቃቅን ጥፋቶች ትኩረት አለመስጠት።
3. አካባቢን ምቹ ማድረግ፡- ከህፃናት አካባቢ የተወሰኑ ነገሮችን ማራቅ ህፃናቱ እንዳይደርሱበት ያደርጋል። መደበኛ የምግብና የእንቅልፍ ሰአት መወሰን አካባቢን ለማመቻቸት ይረዳል። በቤት ውስጥ የሚተገበሩ መመሪያዎችን ህፃናት ምን መቼና እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ

ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ ፦ ቤት ውስጥ ኳስ መጫወት ክልክል መሆኑን፣ ጨዋታ ሲጨርሱ መጫወቻቸውን መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ ከምግብ በፊት የምግብ ፍላጎት የሚቀንሱ ጣፋጭ ነገሮች መብላት አግባብ አለመሆኑን ማሳወቅ ያስፈልጋል።

**4.** ህፃናትን ሳይሆን ሁኔታዎችን መቆጣጠር

ህፃናት ወዲያ ወዲህ የመሯሯጥ፣ የመዳሰስና የመንካት መብት ሊኖራቸው ይገባል።የመዳሰስና የመንካት ችሎታ እድገትን ያፋጥናል። ህፃናት እንዳይሮጡ ፣አርፈው እንዲቀመጡ ፣እንዳይዘሉ ወይንም ወንበርና ጠረጴዛ ላይ እንዳይወጡ ከመከልከል ይልቅ የሚንቀሳቀሱበትን ቦታ ወይም ክፍል ማዘጋጀት ይገባል። ለህፃናት መጫወቻ ባዶ ግቢ ወይንም ምቹ ክፍል ከሌለ በወላጅ ጥበቃ በነፃነት የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ በፕሮግራም ማዘጋጀት ይገባል (ለምሳሌ ከቤት ውጪ መናፈሻ ቦታዎች)።

**5.** ህፃናትን መመሪያና ህግ በማውጣት ላይ ማሳተፍ

ህፃናትን ለእድሚያቸው ተገቢ በሆነ በቤት ወይንም ከቤት ውጪ በሚከናወን ተግባር ማሳተፍ ተገቢ ነው። እድሜያቸው ሶስት አመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ህፃናት በዚህ ሀላፊነት ሊካተቱ ይገባል። ህፃናት ሀላፊነት ሲሰጣቸው ለራሳቸው ጥሩ ግምት እንዲሰጡና የተፈላጊነት ስሜት እንዲሰማቸው ይረዳል።

**6.** ለህፃናት ጊዜ መስጠት

በየእለቱ ለህፃናት ጊዜ ሰጥቶ የተለያዩ ተረቶችን ፣ታሪኮችን ማንበብ ፣ማጫወት ጤናማ ግንኙነት ለመመስረት ይረዳል። ይህ አጋጣሚ በርካታ ግድፈቶችን ለማረምና በቂ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ያግዛል።

**7.** ህፃናት በራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ መፍቀድ

አንዳንድ ጊዜ ወላጆች ቁጥጥራቸውን በማላላት ህፃናት በራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ መፍቀድ አለባቸው። በእርግጥ ህፃናት ከመስመር እንዳይወጡ መጠበቁ አስፈላጊ ቢሆንም ከመጠን ያለፈ ገደብ ግን ህፃናቱ በራሳቸው የማይተማመኑና ጤናማ እንዳይሆኑ ያደርጋል።

**8.** *የመረጃ ወጥነት*

*ህፃናት ዘወትር ተመሳሳይና እርስ በእርሱ የማይጋጭ መልእክት ሊደርሳቸው ይገባል።ለምሳሌ፦በአንድ የቤተሰብ አባል በጣም የሚከለከል ነገር በሌላ የዚሁ ቤተሰብ አባል የሚበረታታ ከሆነ ለህፃኑ በጣም ውዥንብር የሚፈጥር ነው። በተመሳሳይ በትምህርት ቤት ልጆች እንዲያደርጉ መምህራን የሚያበረታቱትን ነገር በቤት ውስጥ ወላጅ የሚከለክል ከሆነ በልጆች አእምሮ በጣም ውዥንብር*

የሚፈጥር ነው። ስለዚህም መቼም ይሁን የት አንድን ነገር በተመለከተ ለህፃናት የሚደርሰው መልክት ተመሳሳይ እንዲሆን ወላጅ የሚመለከታቸውን በማነጋገር ማረጋገጥ አለበት። በተመሳሳይ የወላጆች/የመምህራን መመሪያና ስርአት ማስያዣ ወጥ ካልሆነ ህፃናት ለስነስርአት ትኩረት ለመስጠት ይቸገራሉ።

**9.** የህፃናትን ስርአት አክባሪነት ወላጅ  እውቅና ሊሰጠው ይገባል

ወላጆች የህፃናትን ስርአት አክባሪነት በመለየት እውቅና መስጠታቸው (ልጁን በማበረታታት፣ በመሳም፣ በማቀፍ፣ በማመስገን፣) ህፃናቱ በያዙት ስርአት አክባሪነት እንዲቀጥሉ ያግዛቸዋል።

**10.** ማዕቀብ ማስቀመጥ

በህፃናት ወይንም በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለመከላከል ህፃናት ከአንድ አካባቢ እንዲርቁ ወይንም የተለያዩ ተግባራትን እንዳያከናውኑ ማድረግ ይቻላል። የማዕቀቡ ጊዜ በጣም ረዥም ሆኖ ህፃናቱ የችግሩን ምንነት እንዳይረሱት መጠንቀቅ ግን ይገባል።ለምሳሌ፦ለሶስት አመት ልጅ ሶስት ደቂቃ ፤ ለአራት አመት ልጅ አራት ደቂቃ ያህል ከተፈለገው አካባቢ እንዲርቁ በማድረግ ማእቀብ ማስቀመጥ ይቻላል።

- ○ ከሶስት አመት በታች ላሉ ህፃናት ይህ ዘዴ አይሰራም። ምክንያቱም የማዕቀቡን አላማ ሊገነዘቡት ስለማይችሉ።
- ○ ይህ የማረሚያ ዘዴ ተግባራዊ የሚሆነው ህፃናት ተደጋጋሚ የማይፈለግ ባህርይ ሲያሳዩ ነው። በተጨማሪም ይህ ማረሚያ ዘዴ ተግባር ላይ ከመዋሉ በፊት ለህፃናቱ ስለዚህ ማእቀብ በተደጋጋሚ ሊነገራቸውና እንዲስማሙበት፤እንዲጠነቀቁበት ሊደረግ ይገባል።

ለምሳሌ፦ ህፃኑ በምንም ምክንያት ይሁን በተደጋጋሚ የሚከተሉትን ባህርያት የሚያሳይ ከሆነ

- እቃዎችን መሰባበር፣
- ራሱን ወይም ሌሎች ህፃናትን መጉዳትና ከድርጊቱ ለመቆጠብ ፈቃደኛ ያለመሆን፣
- ወላጆች/መምህራን በሚወያዩበት ወይንም ስራ በሚሰሩበት ወቅት በተደጋጋሚ ማቋረጥ ወይንም በመረበሽ አለማሰራት ፤ወዘተ

ሲያጋጥም ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል።  ለህፃናት ይህን የማረሚያ ዘዴ በተመለከተ ግንዛቤው እንዲኖራቸው ከሁለት አመት ተኩል እድሜ ጀምሮ ማወየት ያስፈልጋል።

**11.** አደጋዎችን ማስገንዘብ

*ህፃናት ለሚያደርጉት ድርጊት ሀላፊነት እንዲወስዱ ድርጊታቸው የሚያስከትለውን አደጋ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።*

**12.** **.** *ልጆቻቸው እንዳያደርጉ የሚያስተምሩትን ነገር ወላጆች ራሳቸው ይህንን ነገር ባለማድረግ አርአያ መሆን አለባቸው።*

*ህፃናት ከወላጆቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው የሚያዩትንና የሚሰሙትን ስለሚተገብሩ፤ እንዲሁም ህጻናት ከሚሰሙት ይልቅ የሚያዩትን መያዝ ስለሚቀናቸው ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያዙትን ራሳቸውም መፈፀም አለባቸው።*

**13.** *ፈተናን ማራቅ*

*ህፃናት እንዳይነካኩ የምንፈልገውን ነገር ከአካባቢያቸው ማራቅ "አትንካ፤ ተው" ከማለት የተሻለ አማራጭ ነው።*

## 5. ቁልፍ መልእክቶች

> አወያይ
>
> እባክዎትን ለተሳታፊዎች ቁልፍ መልእክቶችን ያንብቡላቸው

- ህፃናት ስነ ስርአት ያላቸው ሆኑ ማለት በወላጅ የሚጠበቅባቸውን ጠባይ አሳዩ ማለት ነው።
- ህፃናትን በአዎንታዊ ስነ ስርአት ማስፈኛ መንገዶች ለመግራት ወላጆች ለተወሰኑ ቀናት ሳይሆን ለረጅም ጊዜያት ያለ መታከት በሚያካሂዱት ጥረት ውጤትን ማስመዝገብ ይችላሉ።
- ወላጆች በተለያዩ ሁኔታዎች ወቅት ህፃናት ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ከመንገር በዘለለ በተግባርም በማሳየት አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል።
- ህፃናት ተፈላጊ ጠባያትን ማሳየት ወይንም መፈፀም ካልቻሉ በአወንታዊ የስነ ስርአት ማስፈኛ መንገዶች ማስተካከል ይገባል።
- ህፃናትን አካላዊ በሆነ የቅጣት ዘዴም ሆነ ስሜታቸውን በሚጎዳ መልኩ የምንቀጣ ከሆነ በረጅም ጊዜ በህይወታቸው ላይ መጥፎ ተጽእኖ ሊያደርስባቸው ይችላል።

- ቅጣት ህፃናት በፍራቻ ምክንያት ተገቢ ያልሆነ ጠባይን እንዳይደግሙት ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን የሚያስፈራራቸው ሰው በማይኖርበት ጊዜ ወደማይፈለገው ባህርይ የመግባት እድላቸው ሰፊ ነው።
- የስነ ስርአት ማስያዝ ዋነኛው ግብ መሆን ያለበት ህፃናት ጤናማና በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸው ጠባያትን በፍላጎት እንዲተገብሩ ማስቻል እንዲሁም የህፃናት እድገትና በራስ መተማመንን ከፍ ማድረግ ነው።
- አወንታዊ ስነ ስርአት የማስፈኛ መንገድ ህፃናት በመፍራትና በመሸማቀቅ ሳይሆን በፈቃደኝነት ተገቢ ጠባያትን እንዲከተሉ ያደርጋል።
- ቅጣት አወንታዊ የሚሆነው በቅጣቱ ሳቢያ በህፃናቱ ላይ አካላዊ ህመምና ሌሎች ጉዳቶችን የማይፈጥር ወይም አእምሯዊ ጉዳት የማያስከትል ከሆነ ነው። በተጨማሪም ቅጣት አወንታዊ የሚሆነው ህፃናት በማረሚያው አስፈላጊነት በደንብ እንዲዘጋጁበት ተደርጎና ለሚያደርጉት አላስፈላጊ ባህርይ ቅጣት እንደሚያስፈልገው እነርሱም ተስማምተውበት ከነበረ ነው።
- አሉታዊ የስነ ስርአት ማስፈኛ መንገዶች አደገኛ ከመሆናቸው የተነሳ ህፃናት የበለጠ አመፀኛ እንዲሆኑ የመገፋፋት አቅም አላቸው።
- አወንታዊ ስነ ስርአት ማስፈኛ መንገዶችን የሚጠቀም ወላጅ ወደ መቅጣት/ቅጣት/ የሚሄድበት እድል የጠበበ ነው።